በወጣው የደመወዝ እስኬል አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 2/ለ/ ስለተደነገገና ተጠሪው ደግሞ ይህን የደመወዝ ጭማሪ ክስ ከማቅረባቸው በፊት ጥር 28 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሥራ ክር/መ/ቁ/4544 የተሰጠው ውሣኔ ተጠሪው ካሣ ተከፈሎአቸው ከድርጅቱ እንዲሰናበቱ የተወሰነ በመሆኑ ተጨማሪ ደመወዙን የሚጠይቁበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም እነዚህ ተጠሪው በሰበር መልሳቸው የጠቀሱዋቸውና የሥር ፍ/ቤትም ለውሣኔው መሠረት ያደረጋቸው የሕብረት ስምምነቱና የደመዝ ስኬል አፈፃፃም መመሪያ አንቀፆች ለተጠሪው መብት የሚሰጡ ባለመሆናቸው የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜውን ለማቋረጥ ምክንያት የሚሆኑበት መንገድ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤትም በሰጠው ውሣኔ ድርጅቱ ለከሣሹ /የአሁን ተጠሪ/ መብታቸው በጽሑፍ ያወቀላቸው በመሆኑ ክሱ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 164/3/ መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57049 ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24175 ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፤ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 34011

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሒሩት መለሠ
መድህን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ
ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- እልፍነሽ አማረ - ወኪል ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ አማረ - ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አመልካች የጋራ እናተቸውን የውርስ ሀብት ይዘው ስለሚገኙ የንብረቶቹን ግማሽ 47737.50 (አርባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት ከሃምሳ ) እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጡት መልስ የግራ ቀኙ እናት የሞቱት ግንቦት 17 ቀን 1987 ዓ.ም ስለሆነ ከሞቱ 11 ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤትም የተጠሪ ጥያቄ የበፍ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥያቄው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ 1000/1/ ተፈፃሚነት የለውም ጉዳዩ መታየት የነበረበት ከፍ/ሕ/ቁ. 1000/2/ ጋር ተገናዝቦ ነው በማለት የተጠሪ ክስ በይርጋ ስለማይታገድ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ የውርስ ንብረት በመካፈል ከ11 ዓመት በኋላ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ አይታገድም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ቀርበው ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪ ክስ የመሠረቱት ከእናታቸው በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ቤትና ሌሎች ንብረቶች ለመካፈል ነው፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ በይርጋ አይታገድም ያለው ተጠሪ ያቀረቡት የውርስ ክፍፍል ጥያቄ የማይንቀሣቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1000/2/ መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት ነው፡፡ ይኸው ፍ/ቤቱ የጠቀሰው የፍትሐብሄሩ ድንጋጌ "እንደዚሁም ሟች ከሞቱበት ወይም ከሣሹ በሙብቱ ለመሥራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አሥራ አምስት ዓመት ካለፈው በኋላ፤ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በቀር የተባለው የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን ተቀባይነት አያገኝም፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ አኳያ በይርጋ የማይታገደው "ከዘር የወረደ ርስት" መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ ሊነሣ የሚገባው ቤት የማይንቀሣቀስ ንብረት በመሆኑ "ርስት" ነው ሊባል ይችላል አይችልም የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም ርስት የሚለው ቃል በፍ/ሕጉ ውስጥ ከተካተቱ ድንጋጌዎች ምን ማለት እንደሆነ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1130 የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች የመሬት ርስቶችና ቤቶች ናቸው በማለት የስቀምጣል፡፡ ከዚህም ድንጋጌ ርስት የሚለው ቃል መሬትን የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚሁም ስለ ንብረቶች በሚናገረው የፍ/ብሔር ሕጉ ክፍል የሚገኙት የተለያዩ ድንጋጌዎች ርስትን ከመሬት ጋር የሚያያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ርስት የሚለው ቃል "1. ቤተ ዘመድ የሆነ እያረሠ የሚጠቀምበትና ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ የመሬት አጽመ ርስት 2. የግል ወይም የራስ ይዞ የሆነ ቦታ፣ መሬት" በማለት ትርጓሜ ይሠጠዋል፡፡ በመሆኑም ከተለያዩ የፍ/ሕጉ ድንጋጌዎችም ሆነ ከአማርኛው ትርጉም ርስት መሬት እንጂ ቤትን የማይመለከት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡



ወደ ፍ/ሕ/ቁ 1000/2/ ስንመጣም "... ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በቀር ..." የሚለው ሀረግ በተለይ ከፍ ሲል ከተገለፀው የአማርኛ ትርጉም ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት ከሚለው ጋር የሚጣጣም መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከዚህ ተነስተን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የሟች ቤት ርስት ነው ወደሚለው መደምደሚያ የደረሰውና ክርክሩ በፍ/ሕ/ቁ. 1000/2/ መሠረት በይርጋ አይቋረጥም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 394/98 ኀዳር 5 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የሰሜን ሸዋ መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10940 በሐምሌ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ